# ከኤርትራ የግንቦት ሰባት ሊቀመንበር ዶክተር ብርሀኑ የሰጡት መግለጫ ምን ማለት ነው?

ከእለኔ አለሙ።

ቀደም የአርበኞች ግንቦት ሰባት አሁን ተመልሰው የግንቦት ሰባት ሊቀመንበር የሆኑት ዶክተር ብርሀኑ ነጋ በብቸኝነትና በባለቤትነት በያዙት ራዲዮና ቴሌ ብጅን አመካኝነት አንድ ንግግርና አንድ ቃለ መጠይቅ ኤርትራ ላይ ሁነው በአንድ ሳምንት አድርገዋል ። ይህ ንግግራቸውና ቃለ መጥያቃቸው ምን ያመለክታል ? ምን ለማለት ነው የተፈለገው? የሚለውን ከማየታችን በፊት ወደ እርሳቸው ንግግር እናምራ።

በእሳት ራዲዮና ቴሌ ብጅን የቀረበው ዶክተር ብርሀኑ ነጋ በእንግድነት የተገኙበት ና ንግግር አደረጉበት የተባለው በትህዴን ሁለተኛ ጉባኤ ላይ ነው ትዝብት ያለኝ። ስለ ዶክተሩ ንግግር ከመተቸቴ በፊት ጉባኤ ስለተባለው መናገር እፈልጋለሁ ። ይህ የትህዴን ሁለተኛ ጉባኤ ተጀመረ የተባለው ከዘጠኝ ወር በፊት የድርጅቱ ሊቀመንበር የነበረው ሞላ አስጎዶም ብዛት ያላቸውን የትህዴን የሠራዊት አባላት አስከትሎ የሻቢያ ሠራዊትን ሰብሮ እጅን ለህዋት ወያኔ መንግሥት በሰጠ ከአንድ ወር በኃላ የተጀመረ ነው። ይህንንም የእሳት ራዲዮና ቴሌብጅን በጊዜው በሰበር ዜና አብስሮልናል። በታሪክ ውስጥ የለለ በየትኛውም ንቅናቂ በተለይ በሃገራችን በተደረገው የሽምቅ ተዋጊዎች በነጀብሀ፣ሻቢያ፣ህዋት ወያኔ ወይም ኢህአሰ፣ኢዲዩ፣ኦነግ ወዘተ የሽምቅ ውጊያ ታሪክ ውስጥ ከፍተኛው የጉባኤ ቀን የተደረገበት ቢበዛ ሁለት ቀን አይበልጥም። እንኳን እንደ ትህዴን አይነት የሽምቅ ውጊያ የሚደርግ የተወሰነ ግብ አለው የሚባል ድርጅት ቀርቶ ሀገር የሚስተዳደር መንግሥት እንኮ እንደ መንግሥት ከአራት ቀን በላይ አገራዊ ጉባኤ አይወስድም። ይልቁንም አንድ የሽምቅ ውጊያ የሚካሄድ ሠራዊት ከጉባኤ የፖለቲካ ዲስኩር ይልቅ በወታደራዊ ትዕዛዝ የሚከናወን ስለሆነ ያለው ተግባር ለዚህን ያህል ወራት ጉባኤ አይቀመጥም ። እኔ ባለኝ መረጃ ከትግራይ ህዝብ የወጣ ትህዲን የሚባል ጦር የለም። ጥቂት በህዋት ወያኔ ያኮረፉ የትግራይ ሰዎች ነበሩ እነርሱም ከሞላ አስጎዶም ጋር ገብተዋል። ትህዲን በትግራይ ሕዝብ የሚታወቅና ማህበራዊ መሰረት የሌለው መሆኑ የሚታወቀው ትህዲን ወኪል ነኝ የሚል አንድም የትግራይ ተወላጅ በየትኛውም የዓለም ክፍል አለመኖሩና

አለመገኘቱ ነው። ህዋት ወያኔ ሽምቅ በጀመረ በሶስት ዓመቱ 4500 ሕዝባዊ ሠራዊት እያለው በአፍሪካ ከሁሉም የጎረቤት ሀገሮች እንዲሁም ደቡብ አፍሪካ፣ናይጄሪያ፣ ኡጋንዳ በሁሉም የአረብ አገሮች፣አዉሮፓ ና ሰሜን አሜሪካ በአጠቃላይ 149 የተሞላ ጽህፈት ቤትና በሰነ ሥርዓትና በግልፅ የትግራይ ህዝብ ይደግፋቸው ነበር። ይህ በሀገር ቤት በህብዕ ከሚረዳቸውና በመረጃና ደህንነት ከሚገለግላቸው የሰው ኃይል በተጨማሪ ነው።ህዋት ወያኔ በዚህ ውስን ሠራዊት ያን ያህል ድጋፍ ከነበረው ሰላሳ ሺ ሠራዊት አለው እየተባለ የሚነገርለት ትህዲን በአስራ አምስት ዓመት ቆይታው ከፍተኛ የሆነ የትግራይ ህዝብ ድጋፍ፣ ወኪሎችና ጽሕፈት ቤት በመላው አለም ሊኖረው ይገባል። የትህዴን ሰራዊት ቁጥር ከሰላሳ እስከ አርባ ሺ ነው ተብሎ ከተነገረ ያ የሚሳየው ከማንኛውም የሀገሪቱ ዜጎች በተለይም ከአማራውና ከኦሮሞ ህዝብ በላይ የትግራይ ህዝብ ህዋት ወያኔን በግንባር ቀደምነት እየተዋጋና እየታጋለ ያለ እርሱ ነው ማለት ነው። ይህ ማለት ለህዋት ወያኔ መኖር ለዚህ አምባገነን መንግሥት መሰረቱ የትግራይ ማህረተሰብ ሳይሆን አማራውና ኦሮሞው ነው ማለት ነው። ከዚህ ዘለል አርገን ብናየው የትግራይ ሕዝብ የእርሱ ልጆች ሀገሪቱን እየመሩና እየገዙ ባለበት ዘመን አንድም ተጠቃሚ አይደለም እንደማለት ነው። ስለዚህ ኤርትራ ያለው በትህዴን ስም የተደራጀው ጦር ኢሳያስ አፈወርቂ ለተለየ ግዳጅ ያዘጋጀው የኤርትራ ጦር ነው።አዛዥም ናዛዥም የኤርትራ መከላከያና የደህንነት ጽሕፈት ቤት ብቻ ነው። ወደ ተነሳሁበት ጉዳይ ልግባ። ከእሳት ራዲዮና ቴሌብዥን እንደታየው የትህዴን ሁለተኛ ጉባኤ ከሚካሄድበት ቦታ ላይ ዶክተር ብርሀኑ ነጋ ከአንድ አግድም የእንጨት ወንበር ከተቀመጡ ሰዎች መሀከል ሄዶ መሀከላቸው ሲቀመጥ ያሳያል። ከእነዚህ ከአግድሙ ወንበር ከተቀመጡት ስድስት ሰዎች ሌላ ምንም አይነት ሰው የለም። ዶ/ር ብርሀኑ በጥሩ ሜካፕ ተደርጎለት በርህኛ አስመስሎታል የለበሰው ቲሸርትና ሱሪ የጦር ሠራዊት አፈርማ ሲሆን ኮፍያውም ተመሳሳይ ነው። ዶክተሩ ሄዶ እንደተቀመጠ ወዲያውኑ የመድረክ አስተዋዋቂው ወደ መድረክ ሲወጣ በአንፃሩም ጭብጨባና ጭሆት የሚሰማው ድጂ ቦታውን ያዘ። አስተዋዋቂው የተከበራችሁ የጉባኤ አባላት አሁን ጀግናው፣አርበኛው ብትፈልጉ ዶክተር በሉት ብርሀኑ ነጋ ይናገራል ሲል ድጀው የተዘጋጀውን የጭብጨባና የጩህት ድምፅ ከፈተው። ዶክተር ወደ መድረክ በመውጣት የኮሜዲ ትያትር ያለው ንግግር

ማድረግ ጀመረ። ዶክተር ብርሀኑ ብዙ የሠራዊቱ የጉባኤ አባላት እንዳሉ የተለያዩ የሀገርና የውጭ አገር እንግዶች እንደተገኙ በማስመሰል ነበር ንግግር የጀመረው። በተጨማሪ የተለያዩ የዓለም ጋዜጠኞችም እንዳሉ ከፍተኛ የካሜራ ፍላሽ በዶክተሩ ፊት ላይ ይንፀባረቅ ነበር። ዋናው ነገር የኤርትራ ደህንነት ጽ/ ቤት ከዶክተር ብርሀኑ ነጋ ጋር በመምከር ይህን ቲያትር ለማዘጋጀት  የፈለገበት ምክንያት ምንድን ነው? ምን  መልእክት ለመፍጠር ነው የተፈለገው ?የተዘጋጀው ቲያትር  የተቀነባበረና የታሰበበት ባለመሆኑ ምን ችግር ፈጠረ የሚለውን እንይ። የዶክተር ብርሀኑ ዋነኛውና ማነጣጠሪያው ሀሳብ በአራት ወራት በላይ ያስቆጠረው የወልቃይ የአማራ የማንነት ጥያቄ ስር ሰዶ ከፍተኛ የሆነ ህዝባዊ ማእበልና አመፅ ፈጥሮ ህዝቡ በህዋት ወያኔ ሰላዬች ሁብትና ንብረት ላይ ከዚያም በአጋዚ ወታደሮች ላይና ሰላዬች ላይ የማያዳግም እርምጃ ወስዶ ትግሉ በመቀጠል ወደ ጎጃም ባህር ዳር ደብረ ማርቆስ ፍኖተ ሰላም በአጠቃላይ ጎንደርና ጎጃም የህዋት ወያኔን አስተዳደር አፍርሶ የእራሱን የጎበዝ አለቃ እየመረጠ ሲታገል ህዝቡ የት አለ አርበኞች ግንቦት ሰባት? የት አለ የብርሀኑ ነጋ ጦር ? የት አል? የሚውን የህዝብ ጥያቄ ለመሸንገልና ለማጭበርበር በሚል የታሰበ ቅንብር ነው ። አይ! እኛ እኳ ጉባኤ ላይ ስለነበር ነው። ጉባኤው ወሳኝ ሰለነበር ነው በሀገሪቱ የሕዝብ አመፅና ተቃውሞ  መድረስ ያልቻልነው የሚለውን ስሜት በሕዝብ አይምሮ ለመቅረፅ የተሞከረ ደካማ ቲያትር ነው።ሻቢያና ግንቦት ሰባት የኢትዮጵያን ህዝብ አይምሮ በጣም ይንቁታል ። በተለይ ብርሀኑ ነጋ የኢትዮጵያን የፓለቲካ እሌት ቤቱ ውሰጥ እንደሚሳድገው ውሻ  ንቆ ሲቀልድበት የሚንጨበጭብለት መሆኑን ያውቃል። የማይጠይቅ የማይመረመር ያሉትን የሚቀበል የጠየቁትን የሚሰጥ መሆኑን ስለሚውቅ አይቸገርም። እርግጠኛ ነኝ ኤርትራዊን አድጊ( አህያ) ብለው ቢሰድቡት  ይገባዋል እንደሚል። ጦሪ በመተማ! በአርባ ምንጭ!በአርማጭሆ እየተዋጋ ነው ስለው አዎ እየተዋጋ ነው የሚለኝ ሕዝብ፣ ጦሪ ከኤርትራ ወጦ በሁሉም የአገር  ግዛት ገባ  ስለው አዎ ገብቷል የሚል፣ እንደ አብዮት በፈነዳው የአማራ የአመፅ ንቅናቂ ያልተገኘሁት ጉባኤ ላይ ነኝ ብለው የማይቀበለኝ ምንም ምክንያት አይኖርም ብሎ አስልቶ የሰራው ቲያትር ነው። በዚሁ ቲያትር ሌላው ራሱን ያጋለጠበት አካሄድ ግንቦት ሰባት ከአርበኞች ግንባርና ከትህዲን ጋር ግንባር ፈጠርኩ በማለት የግንባሩ ሊቀመንበር

ዶክተር ብርሀኑ ነጋ ምክትል ሊቀመንበሩ የትህዴን ሊቀመንበር የነበረው ሞላ አስጎዶም እንደሆነ ሆላም ሞላ በስልጣን ጥም ተናዶ ጦሩን ይዞ ወደ ህዋት ወያኔ እጅን ሲሰጥ  የትህዴን ምክትል ሊቀ መንበር የነበረው የግንባሩ ምክትል ሊቀ መንበር በመሆን ያለምንም እንከን ግንባሩ እየሰራ እንደሆን ተገልፆልን ነበር። አሁን ከዶክተር ብርሃኑ ንግግር የተረዳሁት ግንባር የሚባል ከትህዴን ጋር እነዳለነበረውና እንደለለው ያሳያል። በተጨማሪ  በአለፈው ወር በተከታታይ የአርበኞች ግነባር ከግንቦት ሰባት ጋር  የነበረው ቅንጅት ፈርሶል በማለት መግለጫ ማውጣቱ ይታወቃል ።

ሌላው ዶክተር ብርሀኑ ከኤርትራ ሁኖ በእሳት ራዲዮና ቴሌብጅን የሰጠው ቃለ መጠይቅ ነው ። ቃለ መጠይቁ የኢትዮጵያ መንግሥት ህዋት ወያኔ የእንነጋገር ና እንደራደር   መልዕክት ለግንቦት ሰባት ሽምግልና ተላኩብን  በሚል በቀረበ ጉዳይ ነው። ይህን ቃለ መጠይቅ ከማየቴ በፊት አንድ ኤርትራዊ ጓደኛዬ ከአትላንታ ደወለልኝና ቴሌ ፎኑን እንዳነሳሁት በጣም ያለማቆረጥ ይስቃል። ምን ሆንክ? ምነ ሁነህ ስለው አሁንም ይስቃል።  ሳቁ አሳቀኝና እኔም  ነገሩ ሳይገባኝ መሳቅ ጀመርኩ የጎደኛየ ባለቤት እንዲህ ሲስቅ ስለማላውቅ ግራ ገባኝ ። ከዚያ በዚያ ኮልታፉ አፉ  የዶክተር ብርሀኑ ነጋ እንተረቢው ሰምተሽዋል ወይ አለኝ ሳግ እየተናነቀው አልሰማሁትም አልኩት አሁንም መሳቅ ጀመረ ምንድን ነው? ምን ብሎ ነው? ብዬ ጠየኩት አሁንም ስማው አለኝ ተናደድኩና ካልነገርከኝ ለምን ደወልክልኝ አልኩት ? ስማው አለና እንደማሰብ ብሎ በቃ የምንሰድባችሁን ስድብ አይነት ነው የሰደባችሁ አለኝ ።ምን ማለትህ ነው ? አልኩት ቆጣ ብዮ  አይ አለኝ ይህን የእርሱን ቃለ መጠይቅ የሚምን ካለ እኛ አድጊ የምንለው አይነት ፍጡር መሆን አለበት ብየ      ነው አለኝ። ተናድጄ ቴሌፎኑን ዘጋሁና የዶክተር ብርሀኑን ነጋ እንተረቢው ማዳመጥ  ጀመርኩ ስጨርስ እኔም እንደ አማኑኤል መሳቅ ጀመርኩ። አሰብኩና አማኑኤል ይህን የሚቀበልና ዶክተሩም ያምኑኛል ብሎ የተናገረው ለአድጊዎች ነው ያለው ጆሮዬ ላይ አቃጨለብኝ። እውነትም ተንቀናል አልኩ። ለመሆኑ ዶክተር ብርሃኑ  ከህዋት ወያኔ መንግሥት የእንነጋገርና የእንደራደር  መልዕክተኛ ተላከብኝ ሲሉ ምን መልእክት ለማስተላለፍ ነው የፈለጉት? የዚህ ድራማ አስፈላጊነት ፈጠራ ለምን አስፈለገ? የሚለውን እንይ።

ሁላችንም እንድምንረዳው ሁለት አይነት ድርድር አለ በግልፅ የሚደረግ ድርድርና ከመጋረጃ በሰተጀርባ የሚደረግ ድርድር ።የድርድሩ ዓይነት የሚወሰነው እንደ ተደራዳሪዎችና አደራዳሪው ስምምነት ነው። የግንቦት ሰባት ሊቀመንበር ዶክተር ብርሀኑ ነጋ ህዋት ወያኔ ድርድር ላከብኝ የሚለው ይህ ለሁለተኛ ጊዜ ነው። ሁለት ጊዜም በግልፅና በኦፊሻል በእሳት ራዲዮና ቴሌ ብጅን መግለጫ ሲሰጥ ድርድሩና ለድርድሩ መልዕክተኛ የተላኩትን አይናገርም። የሚደርገው ቢኖር የቀጣፊና የወረደ ፕርፓጋንዳ ለመስራት ነው የሚሞክረው ።ያም ሆነ ይህ ያለፈው ሳምንት ስለ ድርድር ማውራት የፈለገበት በሁለት ምክንያትነው።

አንደኛ ዶክተር ብርሀኑ ነጋ በትህዲን ሁለተኛ ጉባኤ እንደ ተገኘና ንግግር አደረገ የተባለው ቲያትር ያልተዋጠለት ቲያትር መሆኑን የሻቢያ ደህንነትና የዶክተሩ ባለሟሎች ነግረውታል። ይህ የዶክተሩ ንግግር ባዶ እስቴጅ ላይ አንድ አስተዋዋቂ እና ድጀ ተዘጋጅተውለታል ያደረገው ንግግር ከመድረኩ ቅንብር እስከ መልእክቱ ተበላሽቷል ። መልዕክቱ ግንቦት ሰባት አሁን ባለው የህዝብ አመፅና ተቃውሞ ለየለለሁት አጋር ድርጅቴ ትህዲን ጉባኤ ላይ ስለሆነ ነው የሚለውን መላ ለመፍጠር ታስቦ የተደረገው ንግግር የኤርትራ ደህንነቶችንና የግንቦት ሰባት መሪዎችን አበሳጭቷል ። ይህ ንግግር አሁን ባለው ህዝባዊ እንቢተኝነትና አመፅ በዚህም በሚመጣ ለውጥ በቀጥታ ግንቦት ሰባትን ከጨዋታ ውጭ የሚደርግ የሚዳርግ የምስክርነት ንግግር ስለሆነ ይህን የሚሻሽል አስቸኳይ ቃለ መጠይቅ በማስፈለጉ ይህ የእንደራደር እና የእንነጋገር የፈጠራ ቃለ መጠይቅ ተዘጋጀ። ችግሩ ዶክተር ብርሀኑ ነጋ ድርጅታቸው ግንቦት ሰባት አንድ ስህተት ና ቅጥፈት ሰርተው እንደገና ያን ለማሻሻልና ለመለወጥ የበለጠ ጥፋትና ቅጥፈት ይሰራሉ ። በውሸት የቆመ ቤትና ድርጅት ሲዋሽ ይኖራል። ዶክተር ብርሀኑ በአማራውም በኦሮሞውም ሕዝባዊ አመፅ ያልተሳተፍነው በጉባኤና በስብሰባ ያልተሳተፍነው ቤዜ ሁነን ነው ብለው ለማስተላለፍ የሰሩት ፊልማ እንዳልተዋጣ ሲውቁ ለሚድያቸው ያቀረቡት ሌላው ቲያትር መሳቂ አደረጋቸው ።ዶክተር ብርሀኑ ከህዋት ወያኔ ቀረበልኝ ላሉት የእንነጋገርና የእንደራደር መልዕክት ለማስተላለፍ የፈለጉት መልዕክት ከወልቃይት እሰከ ጎንደር ከባህርዳር እስከ ሞጣ ከአዲስ አበባ እስከ ለቀምት በአጠቃላይ በአማራ ክልል እስከ ኦሮማይ የሚደረገውን ህዝባዊ ቁጣና አመፅ የምመራው እኔ ነኝ። ይህንም እንደማደርግ የህዋት ወያኔ

መንግሥትም ምዕራባውያንም ያውቃሉ ለዚህ ነው ለእኔ ሽምግልና የተላከብኝ ቢሆንም አይዟችሁ ሌሎች ድርጅቶች አልርሳችሁም አይነት ንግግር ነው ያደረገው። አንድ ነገር ማረጋገጥ የምፈልገው ዶክተር ብርሀኑ ለህዋት ወያኔ አይደለም የዋሸው ። ህዋት ወያኔ ከራሱ ድርጅት በላይ እንደ ሴት አዳሪ ቤት በሩን ከፊተውን ግንቦት ሰባትን በሚገባ ያውቀዋል። ይ ህንን ችሎታውም የድርጅቱን ዋና ፀሀፊ አንዳርጋቸውን ፅጌ ከመያዝ በየጊዜው የሚደረግ ስብሰባ እስከ ማጋለጥ አሳይቶናል ። ግንቦት ሰባት የሚዋሸው ህዝብ ነው። ግንቦት ሰባት የሚቀልደው ነፃነትን ፈልገው በወያኔ አልሞ ተኮሽ እየተገደሉ ባሉ ወጣቶች ደም ነው።ግንቦት ሰባት ቁማር የሚጫዎተው ተጠሪና ቋሜ በሌላው በአማራ ህዝብ ነው። የሃገራችን ገበሪ፣ሙህር!ወጣት ፣ሽማግሌ ፣ሴትና ወንድ ለማንነቱ ና ለነፃነቱ እየተዋደቀ ሠራዊት አለኝ ጦር አለኝ በየትም ቦታና በማንኛውም ጊዜ አለሁ እያለ ሲቀልድ የነበረው ግንቦት ሰባት በጎንደርና በጎጃም የነፃነት ተገዳዮች ምንነቱ ተጋልጧል ። ዶክተር ብርሀኑ የብሶታችን አስለቃሽ እንድትሆን አይደለም አስመራ የሄድከው።በራዲዮ እንተርቢና በቴሌብጅን መሰኮት እየቀረብክ መግለጫ ለመስጠት አስመራ ድረስ መሄድ አይኖርብህም። በቃ ገንዘብ ህዝብ ችሮህል ሰባት ዙር ሠራዊት አሰልጥኛለሁ ብሎህል ። በተግባር አሳየን። የአንተ ፖለቲካ ዲስኩር ሰልችቶናል ሰው ነን ኢትዮጵያውያን ነን አድጊዎች አይደለንም።

ኢትዮጵያ በፓለቲካ ቁማርተኞች
ሳይሆን
በሀቀኛ ልጆቿ ነፃ ትወጣለች !!!